**የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት**

# የሰነድ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎች ሚና በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ

## መግቢያ

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አዋጅ መውጣት እና የሰነድ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መቋቋም በኢትዮጵያ ዘመናዊ የሰነድ ሙዓለ ንዋይ ገበያ እንዲዳብር መሰረት ጥሏል። የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ ቁ.980/2016 (ከዚህ በኋላ "መመሪያው" ተብሎ የሚጠራው) የሰነድ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎችን ጨምሮ ለአስራ አምስት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ አጠቃላይ የፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር ማዕቀፍ ዘርግቷል።
የሰነድ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪ በኢንቨስትመንት ውሳኔዎች ላይ ሙያዊ ምክር በመስጠት በፋይናንስ ሥነ-ምህዳር በተለይ በካፒታል ገበያ አሰራር ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ሀገራችን የተማከለ የሰነድ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ስትጀምር ፈቃድ ያላቸው እና በሥነ ምግባር የታነጹ የኢንቨስትመንት አማካሪዎች መኖር የኢንቨስተሮችን በራስ መተማመን ለማሳደግ፣ የገበያ ተዓማኒነትን ለማረጋገጥ እና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ተሳትፎን ለማሳደግ ያስችላል።
ይህ ጽሑፍ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ውስጥ የሰነድ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎች ሚና፣ ግዴታዎች እና ጠቀሜታን እንዲሁም የህግ እና የቁጥጥር ማዕቀፍን ይተነትናል።

## የቁጥጥር ማዕቀፍ እና ፈቃድ

የመመሪያው መሰረታዊ መርህ ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ የሚመለከተውን የአገልግሎት ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የካፒታል ገበያ ተግባራትን ማከናወን የለበትም የሚል ነው። ይህ ክልከላ በቀጥታ በሰነድ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎች ላይ ተፈጻሚነት ያለው ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረት ከባለስልጣኑ ተገቢው ፈቃድ ሳይኖር ሙያዊ የሰነድ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት ምክር መስጠት ሕገ-ወጥ ነው።

መመሪያው እንደ የሰነድ ሙዓለ ንዋይኢንቨስትመንት አማካሪዎች ሆነው ለመስራት ለሚፈልጉ አካላት እና ግለሰቦች የተወሰኑ የብቁነት መስፈርቶችን ያስቀምጣል። በመመሪያው አንቀጽ 52(1) መሠረት የአክሲዮን ማህበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ የህብረት ሽርክና ማህበር፣ ሁለት አይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማህበር እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር፣ የጸና የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ እና/ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃዶች የያዙ ከሆነ የኢንቨስትመንት አማካሪነት ፈቃድ ለማውጣት ብቁ ናቸው። በተጨማሪ በግለሰብ ደረጃ እድሜያቸው ቢያንስ አስራ ስምንት አመት የሆናቸው ሰዎች በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች የብቃት ማዕቀፍ ውስጥ በተገለጸው መሰረትየምርምር መኮንን የብቃት መስፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነ ለኢንቨስትመንት አማካሪነት ፈቃድ ብቁ ናቸው። ይህ ድርብ የብቃት መስፈርት ተቋማዊም ሆነ የግል አማካሪዎች ጥብቅ የብቃት ደረጃዎችን የሚያሟሉ እስከሆኑ ድረስ በገበያው ውስጥ እንዲሳተፉ ያስችላቸዋል። ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ የኢንቨስትመንት አማካሪ ፈቃድ የማመልከቻ ሂደት ጥብቅ እና ሁሉን አቀፍ ነው። የመመሪያው አንቀጽ 7 ፈቃድ ጠያቂው አካል የፈቃድ ጥያቄውን በሚያቀርብበት ወቅት ማሟላት የሚያስፈልጉትን ሰነዶች ይዘረዝራል።

ከእነዚህ መካከል ለዘርፉ በክፍያ መመሪያው የተቀመጠውን ክፍያ መፈጸም እና ማስረጃ ማያያዝ፣ የንግድ ምዝገባ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ የምስክር ወረቀት ማቅረብ፣ የምስረታ ሰነዶችን ማቅረብ፣ የፈቃድ ጠያቂያ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ አማካሪነት ለመሰማራት በራሱ ቦርድ ያስወሰነ ስለመሆኑ የጸደቀ የቦርድ ውሳኔ፣ የኮርፖሬት መገለጫ እና ዝርዝር የንግድ እቅድ፣ የአመልካቹን ተቋማዊ መዋቅር እና የሪፖርት አቀራረብ መስመር፣ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎችን የሥነ ምግባር ደንብ እና የካፒታል ገበያ ህጎችን ለማክበር የሚገቡ ግዴታዎች ማረጋገጫ ማቅረብ፣ የተረጋገጡ የፋይናንስ መግለጫዎች ወይም ሂሳቦች ማቅረብ፣ ብቁ እና ተገቢ የሆኑ ሰራተኞችን የሚያሳዩ ዝርዝር ማስረጃ፣ ዝቅተኛ የካፒታል መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ እና ሌሎችም መስፈርቶች ይገኙበታል።

## የቁጥጥር ማዕቀፍ እና ፈቃድ

የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱ ወሳኝ ገጽታ አመልካቾች እና ሰራተኞቻቸው ለሥራው ብቁ እና ተገቢ ሰዎች መሆናቸውን መወሰን ነው። የአዋጁ አንቀጽ 56 እና የመመሪያው አንቀጽ 16 የብቁ እና ተገቢ መስፈርቶች በጥምረት የሚታዩ ናቸው። አንድ አመልካች ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪነትን ጨምሮ ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ብቁ እና ተገቢ ለመሆን የብቃት ማዕቀፉን ማክበር፣ በማጭበርበር፣ በስርቆት፣ በእምነት ማጉደል ወይም በገበያ አላግባብ በመጠቀም ጥፋተኛ ሆኖ ያልተገኘ ከሆነ፣ ከካፒታል ገበያ ሥራዎች ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ የማያውቅ ከሆነ፣ የኪሳራ ውሳኔ ያልተላለፈበት ከሆነ፣ ሂሳባቸው በማጣራት ላያ ያልሆነ ከሆነ፣ ከማንኛውም ሙያ ማህበር እና ፈቃድ ካለው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ያልተሰረዘ ከሆነ እና በፍርድ ወይም በህግ ክልከላ ያልተደረገበት ከሆነ ብቁ እና ተገቢ ነው ማለት ይቻላል።

## ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪ የተፈቀዱ እና የተከለከሉተግባራት

ሒየመመሪያው አንቀጽ 54(1) ለኢንቨስትመንት አማካሪ የተፈቀዱ ተግባራትን በዝርዝር የሚያስቀምጥ ሲሆን እነዚህም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመግዛት፣ ለመሸጥ ወይም ለሽያጭ ለማቅረብ የኢንቨስትመንት ምክር መስጠት፣ ስለኢንቨስትመንቶች ትንታኔዎችን ወይም ሪፖርቶችን ማውጣት እና ሌሎች በባለሥልጣኑ የሚወሰኑ ተግባራትን ማከናወን ናቸው። በዚህ ረገድ አማካሪው ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪዎች እንደ ደንበኛ ሳቢ መግለጫ ያሉ የምዝገባ ሰነዶችን በማዘጋጀት ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ኢንቨስትመንት አማካሪ ማከናወን የሌለበት በጥብቅ የተከለከለ ተብሎ ከጠቀሱት ተግባራት አንዱ እና ዋነኛው የኢንቨስተሮችን ገንዘብ በመጠበቅ ወይም በማስተዳደር ሥራ ላይ መሰማራት ነው። እንደ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሮቦ አማካሪ የተለየ ፈቃድ ካልተሰጣቸው በስተቀር የኢንቨስትመንት አማካሪዎች በኤሌክትሮኒክ የታገዘ ዲጅታል የማማከር ዘዴ የኢንቨስትመንት የምክር አገልግሎቶችን መስጠት አይችሉም።

## ከተዛማጅ ሚናዎች ያለው ልዩነት

መመሪያው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ኢንቨስትመንት አማካሪዎችን ሚና ከሌሎች የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች በጥንቃቄ ይለያል። የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎች በዲጂታል ቻናሎች አውቶማቲክ ምክር ከሚሰጡት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሮቦ አማካሪዎች ወይም ለደንበኞቻቸው የኢንቨስትመንት ውሳኔዎችን ከሚሰጡላቸው እና የደንበኛ ፖርትፎሊዮዎችን ከሚያስተዳድሩላቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ፖርትፎሊዮ አስተዳዳሪዎች በተለየ መልኩ ምክር እና ትንተና ከመስጠት ባሻገር ለደንበኞች የኢንቨስትመነት ውሳኔ መስጠት የማይችሉ ናቸው። ይህ ልዩነት እያንዳንዱ አይነት ፈቃድ ያለው ሰው ሊያቀርባቸው ስለሚችላቸው የአገልግሎት ወሰን ግልጽነትን ያረጋግጣል።

## አስተዳደር እና የተሿሚ እንደራሴዎች

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ኢንቨስትመንት አማካሪነት ፈቃድ የተሰጣቸው የንግድ ድርጅቶች በመመሪያው ክፍል አስራ ስምንት ውስጥ ያሉትን የኮርፖሬት አስተዳደር ድንጋጌዎች ማክበር አለባቸው። ከእነዚህ መስፈርቶች መካከል አንደኛው የአስተዳደር ኃላፊነት ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ ማቋቋም ሲሆን ቦርዱ ተገቢ መጠን እና ስብጥር ያለው መሆን፣ ከሥራ አመራሩ የተለየ እና ገለልተኛ የሆነ፣ የቦርድ ሊቀመንበር እና ዋና ሥራ አስኪያጅ/ዋና ሥራ አስፈፃሚ መደቦችን የለየ፣ የሹመት እና ምርጫ ኮሚቴ ጨምሮየአደጋ አስተዳደር እና የህግ ማስከበር ኮሚቴዎችን፣ የኦዲት ኮሚቴዎችን እና ሌሎች አስፈላጊ የቦርድ ኮሚቴዎችን ማቋቋም ይገኙበታል።

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ኢንቨስትመንት አማካሪ ፈቃድ የተሰጠው የንግድ ድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ/ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ዋና የህግ ማስከበር መኮንን በተጨማሪ በባለሥልጣኑ እንደ ተሿሚ እንደራሴ ፈቃድ የተሰጠው የምርምር መኮንን ሊኖረው ይገባል። የምርምር መኮንኑ በመመሪያው አባሪ ሁለት ውስጥ የተገለጹትን የትምህርት ዝግጅቶች እና የሙያ ማረጋገጫዎችን ጨምሮ የተወሰኑ የብቃት መስፈርቶች ሊኖሩት ይገባል። በብቃት ማዕቀፍ (አባሪ ሁለት፣ ሠንጠረዥ 2) መሠረት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በስታቲስቲክስ ወይም ተዛማጅ ዘርፎች የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው፣ በፋይናንስ አገልግሎት ኢንዱስትሪ ውስጥ ቢያንስ ለሦስት ዓመታት የምርምር ልምድ ያለው፣ ለኢንቨስትመንት አማካሪዎች በተዛማጅ ስራዎች የሙያ ማረጋገጫ ወይም ስልጠና የወሰደ፣ የኢትዮጵያ የፋይናንስ ገበያ እና ሰነዶች እውቀት ያለው፣ የፋይናንስ ግምገማ እና የኢንቨስትመንት ትንተና ክህሎቶች ያለው፣ የዳታ ትንተና እና የሞዴሊንግ ችሎታዎች ያሉት ሊሆን ይገባል።

## ዋና የህግ ማስከበር መኮንን

ማንኛውም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪ እንደ ተሿሚ እንደራሴ በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ዋና የህግ ማስከበር መኮንን ሊኖረው ይገባል። ኃላፊነቶቹም በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ሁሉንም የሚመለከታቸውን አዋጆች፣ ደንቦችን እና መመሪያዎች ማክበርን ማረጋገጥ እና ሲጣሱም ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማድረግ፣ የህግ ማስከበር ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሙ አደጋዎችን ለመቀነስ ፖሊሲዎችን ማዘጋጀት እና መተግበር፣ እና ለሠራተኞች አመታዊ የህግ ማስከበር ስልጠና መስጠት ይገኙበታል፣ ማንኛውንም ፈቃድ ያለው ተሿሚ እንደራሴ ከሥራ መሰናበት ወይም ሌላ ቦታ ላይ ለመመደብ ቅድሚያ የባለሥልጣኑ ፈቃድ የሚያስፈልግ ሲሆን መደቡ በምንም አይነት መልኩ ባዶ ሆኖ መቆየት የለበትም።

# የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎች ሚና በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ

## የስነ-ምግባር ደንብ እና የሙያ ደረጃዎች

የመመሪያው ክፍል ሃያ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎችን ጨምሮ ሁሉም የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች መከተል ያለባቸውን አጠቃላይ የስነ-ምግባር ደንብና መሰረታዊ መርሆችንም ያስቀምጣል።

መሰረታዊ መርሆዎችን በተመለከተ በታማኝነት እና ያለ አድሎ ማገልገል፣ በጥንቃቄ፣ ክህሎት እና በትጋት ማከናወን፣ የጥቅም ግጭቶችን ማስተዳደር ወይም መቀነስ፣ ለደንበኛ ሀብቶች እና መረጃዎች ተገቢ የሆኑ ጥበቃ ማድረግ፣ ከደንበኞች እና ከተቆጣጣሪዎች ጋር ግልጽ እና ውጤታማ ግንኙነትን ማድረግ ናቸው። በዚህ ረገድ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ የኢንቨስትመንት አማካሪ ተሿሚ እንደራሴዎች፣ ዳይሬክተሮች እና ሰራተኞች እንደ ማንኛውም የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ የሙያ ማህበራቸውን እና የባለሥልጣኑን ሙያዊ የሥነ ምግባር ደረጃዎችን ማወቅ እና ማክበር፣ ገለልተኝነታቸውን ሊጎዳ የሚችል ጥቅም አለመቀበል፣ የደንበኞቻቸውን ጥቅም ማስቀደም፣ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ አለመስጠት፣ ማንኛውንም ታማኝነት በሚሸረሽር የእምነት ማጉደል፣ ማጭበርበር እና ማታለል ድርጊት ውስጥ አለመሳተፍ አለባቸው።

## የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪ ለደንበኞቹ ያለው ግዴታ

የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎች ለደንበኞቻቸው የተወሰኑ ግዴታዎች አሏቸው። ከእነዚህ መካከል ደንበኞችን ሙያዊ በሆነ መልኩ በተገቢ መንገድ ማስተናገድ፣ ፍትሃዊ እና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ማስተናገድ፣ ደንበኞች ምክር የሚጠይቁበትን ነገር ጋር በተያያዘ ያለውን ስጋት በሚገባ እንዲረዱ ማድረግ እና ማረጋገጥ፣ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ ግልጽ፣ ፍትሃዊ እና አሳሳች ባልሆነ መንገድ ለደንበኞች ማቅረብ፣ በደንበኛው የተወሰኑ የኢንቨስትመንት ዓላማዎች ላይ የተመሠረተ ምክር መስጠት፣ ለአገልግሎቶቹ ተገቢ ክፍያዎችን ማስቀመጥ እና ሁሉንም ክፍያዎች ይፋ ማድረግ፣ በደንበኞች የሚነሱ ቅሬታዎችን በፍትሃዊ፣ ግልጽ በሆነ መንገድበወቅቱ መፍታት፣ ጠንካራ የደንበኛህን እወቅ እና በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝተን በግንዘብ መርዳት ለመዋጋት የወጡ ህጎችን የሚያከብር የአሰራር ሥርዓት መፍጠር እና ደንበኞች ማክበራቸውን ማረጋገጥ እና የደንበኛ መረጃ ሚስጥራዊነት መጠበቅ የሚሉት ይገኙበታል።

በተለይ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎች በፋይናንስ ሁኔታ እና ዓላማዎች ላይ በመመስረት ምክሩ ለደንበኛው ተስማሚ ነው ብለው ለማመን በቂ ምክንያት ሳይኖር የኢንቨስትመንት ምክሮችን አለመስጠት፣ ከኢንቨስትመንት ቁልፍ ባህሪያት ጋር የተያያዙ ሁሉንም ወሳኝ መረጃዎች በበቂ ሁኔታ ይፋ ማድረግ፣ ምክር በሚሰጥበት ጊዜ እውነታዎችን እና አስተያየቶችን መለየት፣ በተቆጣጣሪው እንዲሰጡ የተፈቀደላቸውን የምክር አገልግሎቶች ዓይነቶችን ሁሉ ይፋ ማድረግ፣ ከሰነዶች፣ ማስታወቂያዎች እና ጽሑፎች ጋር በተያያዘ ስለተቀመጡ ማስጠንቀቂያዎች፣ ተፈጻሚነት ስለሌላቸው እና ኃላፊነት ስለማይወስድባቸው ጉዳዮች ለደንበኛው ማሳወቅ፣ የሚቀበለውን ሁሉንም አይነት ክፍያ ለደንበኛው በጽሑፍ ማሳወቅ፣ የደንበኛ ፍላጎቶችን መሰረት በማረግ የተሻለ ምክር ለመስጠት የተቻለውን ጥረት ማድረግ፣ የደንበኛ ትዕዛዞች ስለመፈጸማቸው የሚያሳይ የጽሑፍ ማረጋገጫ ወዲያው ማቅረብ፣ የማማከር ሥራውን ከማቆሙ በፊት ለደንበኞች ያለውን ኃላፊነት በሙሉ መወጣቱን እና ደንበኞች በሌላ አማካሪ አገልግሎት እንዲያገኙ ዝግጅት መደረጉን ማረጋገጥ አለበት።

በቀጣይ ጽሁፍ ቀሪ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪ ሚና ምን ምን እንደሆኑ በጥልቀት የምንቀጥልበት ይሆናል።